በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ - 2

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon4@gmail.com

ቦታ፡- **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሐምሌ ፲፫ ቀን ፳፲፫ ዓ.ም.

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በዚህ ርዕስ ሥር ክርስቲያን ስላልሆኑትና በስም ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳውያን) ስለሆኑት ሰዎች ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ በመቀጠል እውነተኛ (መንፈሳውያን) ክርስቲያኖችን (ኦርቶዶክሳውያንን) እንመለከታለን።

3. ***<u>እውነተኛ ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) - መንፈሳዊ ሰው</u>***

- እንዲህ ያለው ሰው የሚመራው በመንፈስቅዱስ ነው።
- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በተጠመቁበት ዕለት የተቀበሉት መንፈስቅዱስ በውስጣቸውም ያለ ቢሆንም ሁሉም ግን በመንፈስቅዱስ በመመራት የሚኖሩ አይደሉም።
- እውነተኛ ክርስቲያኖች ልክ ምሳሌ እንደሆናቸው እንደአምላካቸው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በራቀ ንጹሕ ሕይወት በውስጣቸው ባለ መንፈስ ቅዱስ መሪነት ይጓዛሉ።
- በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ማንም ሊል አይችልም።
- መንፈስ ቅዱስ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረንን የነገረንን ያንኑ ትምህርት ያስተምረናል።
- መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ከሆነው ወስዶ ያንኑ መልሶ ይነግረናል።

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- መንፈስ ቅዱስ በሰው ሕይወት በሚሠራው ሥራው አማካይነት እኔ የሚለው የሰው አስተሳሰብና አመራር እየከሰመ፡ እየጠፋ የሥጋ ፍላጎ ሰውን የሚቆጣጠርበት አቅም ያጣል፡፡
- ሰውም በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይለወጣል ያድጋል በክርስቶስም ወደ ሆነው ፍጹምነት ይደርሳል፡፡
- የአምላካችን የክርስቶስ ልብ ያገኛል፣ የሕይወት ጎዳናውና ውስጣዊ ሕይወቱም የሚከተለውን ቅርጽ ይይዛል፡፡ «እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን፡፡» *ቀዳ ቆሮ 2፡16፡፡*
  - እኔ ወይም ሥጋዬ የሚሹትን በመተው ሕይወቴን አምላኬ ክርስቶስ ይቆጣጠረው፡፡ ይህም የሚሆነው በእኔ በሚሠራ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡
  - እኔ፣ ሥጋዬ፣ ፍላጌቴ በአምላኬ በክርስቶስ ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡
  - ትኩረቴ ሁሉ አምላኬ ክርስቶስን ደስ በሚያሰኘውና ስለኔም ባለው ዕቅድ ላይ የሆነ ነው፡፡
- የዚህ መንፈሳዊ ሰው ኃይሉ በመንፈስ ቅዱስ ከሆነው ጸሎት፣ የእግዚአብሔርን ቃሉን ከመውደድ፣ ለእግዚአብሔርም ፍጹም ታማኝና ታዛዥ ከመሆን የተገኘ ነው፡፡
- ይህ ሰው የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወቱ ይገለጣሉ፡፡ እነዚህም «ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት፡፡» ናቸው፡፡ *ገላ 5፡22፡፡*
- የዚህ ዓይነት ሰዎች ዋነኛ ምሳሌዎች በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ የጌታችን ደቀመዛሙርት ናቸው፡፡ *የሐዋ 2፡1-ፍም፡፡*

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- እነርሱ በጥበብ፣ በዕውቀት በማስተዋልም ተሞልተው በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ አዲስ ፍጥረት (ሰዎች) ሆነው ነበር፡፡
- በልባቸው የሠለጠነ (የነገሠውን) አምላካችን ክርስቶስን በሕይወታቸው ለብሰው ምሳሌነቱን ተከትለው ነበር፡፡ በዓለሙም ሁሉ እየተዘዋወሩ ‹‹እንደ ራሳችን ኃይልና ፈቃድ ሳይሆን በአምላካችን በክርስቶስ ረዳትነት እናስተምራለን፡፡›› በማለት አስተማሩ፡፡
- በነገሥታቱም ፊት በኃይልና በድፍረት ያለፍርሐት ቆሙ፡፡ በእስር ቤት በነበሩም ጊዜ ልባቸው ሊነገር በማይችል ደስታ ተሞልቶ ነበር፡፡ ‹‹እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፡፡» ***<u>የሐዋ 5፡41፡፡</u>***
- ምንም ዓይነት የሥጋ ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን «በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፡፡ ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር፡፡» ***<u>የሐዋ 2፡46-47፡፡</u>***
- ስለዚህ ወገኖቼ! ሕይወታችንን ለአምላካችን ለክርስቶስ ሰጥተን በፈቃዴ እራባለሁ፣ እጠማለሁ፣ አዝናለሁ፣ ችሎታዬንና የትምህርት ደረጃዬን ሁሉ እተወዋለሁ የምንልበት ድፍረት ይኖረን ዘንድ ይገባናል፡፡

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- እንዲሁም በፍጹም ሙላታችን፣ ሰላማችን፣ ደስታችን ከሁሉም በላይ በስቃይና በመከራ መካከል በሆነ መረዳታችን ደስ ይለን ዘንድ በአምላካችን በክርስቶስ ታምነን ሕይወታችንን አሳልፈን እንስጠው፡፡
- ኃጢአትና የሥጋ ፈቃድ ወጣቱን ቅዱስ ጊዮርጊስን የሃይማኖት አርበኛ እንዳይሆን አላገዱትም፡፡ መርዝ ያለበትንም ነገር እንዲቀበል ቢያስገድዱት ይህም ከክርስቶስ ፍቅር አልለየውም፡፡ ‹‹ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?›› *ሮሜ 8፡35፡፡* እንዳለ፡፡
- አባ ጳውሊ የተናቀውን ምግብ እየቀመሰ፣ ከዚህ ዓለም ከሆነው ነገር በጥቂቱ እያገኘ ከ80 ዓመት በላይ ኖሯል፡፡ ሕይወቱም ሰላምን የተሞላ ነበር፡፡ ጤናና ሰላም የሚገኘው በመብላትና በመጠጣት አይደለም፡፡
- ቅድስት ዲማንያ በመንፈስ ቅዱስ ሆኖ ከአንደበትዋ በወጣው ቃል አባትዋን ከጥፋትና ጣዖትንም ከማምለክ ታድጋዋለች፡፡
- ‹‹እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና፡፡›› *ዕብ 12፡1-2፡፡*
- ወገኖቼ ሆይ! እንደነዚህ ቅዱሳን ፍጹም በሆነው ድል መደሰት ይቻላል፡፡ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና፡፡›› *ሮሜ 8፡2፡፡*

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- አሁን ዋናው ጥያቄ - መንፈስ ቅዱስ በእኔ እንዲሠራ አምላኬ ክርስቶስም በሕይወቴ እንዲከብር (እንዲነግሥ) እና ጠናካራና ድል የማደርግ እንድሆን ምን ላድርግ? የሚል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ልቤን በመለወጥ ከደካማነት ወደ ብርታት ከፍ አድርጎኝ በሕይወቴ እንዲሠራና አምላኬ ክርስቶስን ወደመልበስ እንዲያደርሰኝ ምን ላድርግ? የሚል ነው፡፡

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወቴን ይመራ ዘንድ የእኔ ድርሻ ምንድር ነው?

1. ከሁሉ አስቀድሞ በ40ና በ80 ቀናችን ተጠምቀን ቅዱስ ሜሮንን ስንቀባ በአዲስ ልደት መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልንና እርሱ መንፈስ ቅዱስም በሕይወታችን እንዳለ ማመን ነው፡፡ ‹‹ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡፡›› *ማር 16፡16፡፡*
2. ዘወትር በልበ አምላክ ዳዊት መዝሙር ‹‹ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፥ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ፡፡አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፡፡የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ፡፡›› *መዝ 50(51)፡9-12፡፡* በማለት መጸለይ፡፡
3. በእግዚአብሔርና በመቀጠልም በንስሐ አባታችን በካህኑ ፊት ኃጢአታችንን በመናዘዝ ንስሐ መግባት፡፡ ‹‹በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 1፡9፡፡*
4. ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ይቅርታን አግኝተን ከአምላካችን ጋር መኖር፡፡ *ዮሐ 6፡54-56፡፡*

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወቴን ይመራ ዘንድ የእኔ ድርሻ ምንድር ነው?...

5. የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉሙንም ከትርጓሜው ማንበብና ሲነበብልንም መስማት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መስማት ሕይወትን ይለውጣል፡፡ ‹‹እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፡፡›› *ዮሐ 15፡3፡፡*
6. ሕይወታችንን ስንመራ በእግዚአብሔር ታምነን መራመድ፡፡ ‹‹እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡›› *ቀዳ ጴጥ 5፡7፡፡* ‹‹ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡›› *ቀዳ ጴጥ 1፡13፡፡*
7. ነቢዩ ኤልያስ በእግዚአብሔር ፊት ይቆም ዘንድ ወደ ተራራው ራስ ወጥቶ እንዳደረገው ጫጫታና ሁካታ ካለበት ተለይተን ወደ ጸጥታ መግባት፡፡ ‹‹እርሱም፦ ውጣ፥ በተራራውም ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም አለ፡፡ እነሆም፥ እግዚአብሔር አለፈ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ፥ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከእሳቱም በኋላ ትንሽ *የዝምታ ድምፅ ሆነ፡፡* ኤልያስም ያን በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጐናጸፊያው ሸፈነ፥ ወጥቶም በዋሻው ደጃፍ ቆመ፡፡ እነሆ፡፡ ኤልያስ ሆይ፥ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ፡፡›› *ቀዳ ነገ 19፡11-13፡፡*

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

ሕይወቴ ጥንካሬ ወደሚገኝበት ሲለወጥ ምን ይሆናል?

- ኃጢአትንና ሞትን በማሸነፍ የድል አድራጊነት ሕይወት እንመራለን፡፡ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና፡፡›› *ሮሜ 8:2፡፡* ይህም ድል የሥጋን ሁሉ ፈቃድ ማሸነፍ ነው፡፡ ‹‹ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፡፡›› *ገላ 5:16፡፡*
- ጸሎታችን ከልብ የሚመነጭ ብርቱ ጸሎት ይሆናል፡፡ ‹‹በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፡፡›› *ኤፌ 6:18፡፡*
- አገልግሎታችን ደቀ መዛሙርቱ በአገልግሎታቸው ሲጸልዩ ምድር ትናወጥ እንደነበረው በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ይሆናል፡፡ ‹‹ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ፡፡›› *የሐዋ 4:31፡፡*
- ልቦናችን አምላካችን ክርስቶስ የነገሠበት ይሆናል፡፡ አምላካችን ክርስቶስ በነገሠበት በዚህ በልቦናችን በመስቀሉና በትንሣኤውም ደስ እንሰኛለን፡፡ ‹‹በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፡፡›› *ኤፌ 3:16-17፡፡*

ምን ተማርን?

- ከኃጢአት ተለይተን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሕይወታችንን ስለመምራት፡፡
- በእያንዳንዱ ቀን በአስተሳሰባችን፣ በአመለካከታችንና በድርጊታችን ዘወትር ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች መሆናችንን ራሳችንን በመመርመር ስለማረጋገጥ፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስትና መንፈሳዊ ደስታ የሚገኝበትና የሚደረግበት ነውና ደስ ይለን ዘንድ እንደሚገባ፡፡

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org